ዛሬም ሃቀኛ መስሎ ለመካሸ የሚቃጣው:: "ጉሽ/" የሚለው አጣ እንኳ በዘመነና መደበኛ ስብሰባው ላይ ያምበጨበጨውን ይዞ "ይኸውላችሁ ግም—ገማ/" እያለን ነው:: እኛ መግማቱን አያውቅንም አናወጠን ብለን፣ አፍንጫችንን ወትፈን ከሩቁ አንቆምም:: ይልቁንስ ጥምበኩስ የወጣውን ፋሽስታዊ መንግሥት ጠራርጉ ከመጣል ውጪ መፍትሄ አለ-መኖሩን ተገንዝበን "ይበልጥ በተደራጀ በተቀናጀና በተፋፋመ ትግል እናውድመው/" ነው የምንል:: ዛሬም እንደወትሮአችን::

ባለፉት ዓመቶች ላደረሰብን እልቂትና ውድቀት የምንጠይቀው ምንጊዜም እሱኑ ፋሽስታዊውን መንግሥት ነው:: እዚህ ላይ ወለም ዘለም የለም:: የኢትዮጵያን ሀዝቦች ሰለባቸው ያደረጉትን ከፍ ብሎ የተገለጡትን ከባድ ፖለቲካዊና ወታደራዊ እንዲሁም ማኅበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ቀውሶችና ጠንቆች ራሱ ያላመጣቸው፣ አለዚያም ያላባባሳቸው ለመምሰል፤ ከተጠያቂነትም ለማምለጥ፣ ማላከኪያ ፍለጋ ያነፈንፋል:: ራሱ ለኩሶ "ታይቶኛል ቤት ይቃጠላል/" እንዳለቸው ዐብዲትም መሆን ይቃጣዋል::

—ለሀገሪቷ ነፃነትና ክብር መደፈር፣ ለሕዝቡ ሰቆቃ፣
ተጠያቂዎቹ የፋሽስቱ መንግስትና የሶቭየት
ሕብረት ጣልቃ ገቦች ናቸው/
— የፋሽስቱ መንግስት አዳዲስ ቅጥፈቶችና
ማደናገሪያዎች ይጋለጣሉ//
—ሕዝባዊ ትግል በድል ጎዳናው ይቀጥላል/
—እ ና ቸ ን ፋ ለ ን / /